# የሃገራችን ወቅታዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

ኣሁን በሃገራችን ያሉት ችግሮች በዛ ያሉ ናቸው፣ የተለያዩ ችግሮች ቢሆኑም ኣዲስና ዛሬ የመጡ፣ ከዚህ በፊትም ታይተው የማይታወቁ፣ ወይም መፍትሔ የሌላቸው ችግሮች ኣይደሉም። ቅን ፍላጎት ካለ ቶሎ መፍታት ይቻላል።

መፍትሔዎቹ እነዚህ ናቸው ብለን ከማቅረባችን በፊት ግን በሃገራችን ያሉት ችግሮች ምንድናቸው ብለን መጠየቅና በዝርዝር ለይተን ማስቀመጥ ይገባል። ዋናው ችግር ብለን የምናየው ኣሁን በተለያዩ ቦታዎች በመከሰት ላይ ያለው ለሰላም መደፍረስ ምክንያቱ ምንድነው ብለን በመጠየቅ እንጀምራለን።

ይህ የሰላም መደፍረስ በተለያዩ ቦታዎች የተነሳበት ዋነኛ ምክንያት ከበላይ የሚታይ ምልክት ወይም (ሲምተም symptom) በተለያዩ ጎሳዎች የሚነሳው ግጭት ሲሆን፣ ይህ ከላይ የሚታይ እንጂ ከውስጥ ሌላ ድብቅ ሕመም እንዳለ ግልጽ ነው። ድብቅ ሕመም የምንለውም ኣንድ ብቻ ሳይሆን ተደራራቢ ሕመሞችም ሊኖሩ ይችላሉ። ከነዚህም በስተጀርባ ሌሎች ጥልቅ ምክንያቶች ኣሉ። ሕመሞቹም ከብዙዎቹ በጥቂቱ፦

1. የፌዴራል መንግሥቱ ድክመት
2. የመሪዎች ብቃት ማጣትና የበጐ/የመልካም ኣስተዳደር ጉድለት
3. ሥራ ኣጥነትና ድኽነት፣
4. ከውጭ ሃገር ያሉት ተቃዋሚ ቡድኖች የሚጫወቱት ኣፍራች ሚና፣
5. የሕግ ክፍል ከመንግሥት ኣስፈጻሚው ክፍል ነፃ ያለመሆን
6. የፌዴራሊዝም ኣወቃቀር ጉድለት

ናቸው ብለን ለመነሻ ያህል ብንጀምር ለጊዜው በቂ ነው። የመጀመሪያዎቹ ዐራት ነጥቦች ወቅታዊ ችግሮች ሲሆኑ፣ ኣምስተኛውና ስድስተኛው ደግሞ ወቅታዊ መስለውም ባይታዩ ከውስጥ የተደበቀ በሽታ ሆነው ዘላቂ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸውና በክፍል ሁለት እናቀርባቸዋለን። እንግዲህ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ነጥቦች እንመልከት፦

የጥንቱ የጐሳዎች ችግር ከብዙ በጥቂቱ ተፈትቷል፣ ይኸም ማንም ጐሳ ከዚህ በፊት ያልታየ ነጻነት ኣግኝቶ ራሱን በራሱ የሚተዳደርበት "ክልል" ኣንዳለው፣ የገዛ ጐሳው መሪዎች፣ ዳኞች፣ የፖሊስ ሃይል... ወዘተ እንዳለው ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ እውነትነት እያለው፣ "ክልል" የሚለው ቃል ምን እንደሆነና ምንስ እንደሚያስከትል፣ ኣንድ የኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር በዩ-ትዩብ (Youtube) በሰጡት ገለጻ ዘርዝረውታል። ክልል ማለት በደርግ ዘመን ኬላ

ተተክሎ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ እንኳን ሰው እንዳይዘዋወር በመጠበቅ ቁጥጥር እንደነበረው ዓይነት ባይሆንም በሰው አዕምሮ “ክልል” የሚል ቃል የሚሰጠው አስተሳሰብ ከዚያ ብዙም ያልተለየ ነው። ለዚህም ነው ከዚህ ክልል ዉጡልን እየተባለ አንዱ ጐሳ ከሌላው ጐሳ ሲተራመስና ሲጣላ የሚገኘው። ስለዚህ በሕገ መንግሥቱ ሰነድና በመንግሥት አሠራር፣ በቃልና በተግባር “ክልል” የሚለው ቃል ወጥቶ “ብሔር” ወይም “ቤት” በሚል ቃል ቢተካ የተሻለና ደግ አስተሳሰብ እንደሚያስከትል አይጠረጠርም። አስቀድሞ በሰው አስተሳሰብና አዕምሮ የዋለና ያደረ ነገር ቀጥሎ በተግባርም ይውላል።

ከዚህም ቀጥሎ መንግሥት ለዚህ ጉዳይ ጥብቅ ትኩረት ሰጥቶ በጋዜጣ፣ በሬድዮና ቴሌቪዥን ተደጋጋሚ መልእክት እያስተላለፈ፤ “ሃገር የጋራ ነው፣ ሃይማኖትና ጐሳ ግን የግል ናቸው!” የሚል መርሆ በሕገ መንግሥቱ እንዳለ ህዝቡ እንዲውቀውና እንዲያምንበት ማድረግ፣ ሃገሪትዋን ለሁሉ ኢትዮጵያዊ እኩል የምትደርስው፣ በደማቸውን አፍስሰውና ዓጥንታቸውን ከስክሰው፣ ታላቅ መስዋእት ከፍለው ያቆዩልን የጥንት ወላጆቻችን ከሁሉም ብሔሮች ቅልቅል የተውጣጡ እንጂ የዚህ ወይም የዚያ ብሔር ብቻ እንዳልሆኑ ታውቆ፣ አንዱ ጐሳ ሌላውን ከዚህ ውጣ ማለት ፍጹም እንደማይችል፣ ማንም ኢትዮጵያዊ በገዛ ሃገሩ የመዘዋወር ሙሉ ነፃነት ስላለው፣ ዓቅሙ እስከ ቻለለት ድረስ የትም ብሔር/ቤት ሄዶ ሊነግድ፣ ሊያርስ፣ ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሕጋዊ ሥራ መሥራት እንደሚችል ማሰተማርና በተግባርም እንዲውል ማድረግ፣ ይህንን የሚቃወም ማንም ሰው ሲኖር ደግሞ ተገቢውን ሕጋዊ ቅጣት እየቀጡ ሕዝብን ዘወትር ማስተማር ያስፈልጋል።

ለአንድ ዜጋ የሕይወቱና የንብረቱ ዋስትና የማይጠብቅ የፌዴራል መንግሥት ደካማ ነው። በየብሔሩ በዜጎች ላይ ከባድ ጥቃት ሲደርስ እየታየ የፌዴራሉ መንግሥት ድክመት ተደጋግሞ የተጋለጠው፤ “ክልሉ ራሱ ችግሬን እኔው እፈታዋለሁ ብሏል…” እያለ እጁን አጣጥፎ ሲቀመጥ ነው። የብሔሩ ችግር ብሔሩ ራሱ ቢፈታው’ማ ኖሮ በዜጎች ላይ ግድያና የንብረት መቃጠል፣ ያልሞቱትም እየተባረሩ ለስደት እስከ መዳረግ መቸ በተደረሰ ነበር? ይህ ዓይነቱ በደል ከደረሰ በኋላ ግን የፌዴራሉ መንግሥት የብሔሩን መሪ ሽሮ ብልሽቱን የሚያርም፣ ሰባራውን የሚጠግን መሪ በቶሎ መተካት ይገባዋል።

በመሪዎች ብቃት ማጣትና በበጐ ወይም መልካም አስተዳደር ጉድለት ብዙ ችግሮች ይከሰታሉ። የመሪዎች ብቃት በምን ይለካል? መለኪያው ይህን ትምህርት ተምረዋል፣ ይህንን ኮርስ ወስደዋል… ወዘተ የሚሉት ፈሊጥ ሊሆን አይችልም። ይህ ብቃት የሚለካው በሁለት ነገሮች ነው። የሚያስተዳድሩት

ወይም የሚመሩት ወረዳ ወይም ክፍለ ብሔር በሰላም ሲንቀሳቀስና ሲለማ መገኘቱ ብቻ ነው። ከዚህ የተሻለ ሌላ መለኪያ የለውም። በአንድ ቦታ ሰላም ከደፈረሰ፣ ዕድገትና ልማት ከሌለ፣ የዚያ ቦታ መሪ ብቃት የለውም ለማለት ይቻላል። በጐ አስተዳደር በባለስልጣኖች አፍ እንዲሁ እንደዘፈን ሲደጋገምና ሲወራ መስማቱ፣ እነዚህን ሁለት ነገሮች እስካላካተተ ድረስ ፍሬ ቢስ ነው።

ይህም ወደ ሦስተኛው ነጥብ ይወስደናል፦ ሥራ አጥነትና ድኽነት እንዴት ይወገዳሉ? አንድ የወረዳ ወይም የብሔር መሪ ብቃት ካለው እንደምንም ብሎ የሚያስተዳድራትን ክፍል ሰላም የሚሰፍንባትና የምታድግበትን መንገድ ሌት ተቀን አጥንቶ፣ ፈልጐ፣ ተመራምሮ በተግባር ያውላል። ከዚህ በቀር ሌላ ዓላማ አይኖረውም። ይህንን ከማድረግ ይልቅ ግን የራሱን ኪስ የሚሞላ፣ የራሱንና የቤተሰቡን ጐተራ የሚያዳብር ሆኖ ሲገኝ፣ ማንም የሕዝብ ሃላፊነት የተረከበ የአመራር አባል ከሕግ በታች ነውና፣ በሙስና ተከስሶ መቀጣት ይገባዋል።

አሁን ከዐራተኛው ነጥብ ላይ ደረስን፤ ይህም ከውጭ ሃገር ያሉት ኢሳትና ሌሎች ተቃዋሚ ቡድኖች የሚጫወቱት አፍራሽ ሚና ነው። ከውጭ ሃገር ያሉት ተቃዋሚ ቡድኖች ሁሉም ባይባል፣ ከሞላ ጐደል፣ በግብፅ፣ በሻዕቢያና፣ በድሮ የደርግና የፌውዳል መንግሥት ርዝራዦች ትብብር የሚንቀሳቀሱ ለመሆናቸው በተደጋጋሚ በማስረጃ ታይቷል፣ ተረጋግጧል፣ የሚያጠራጥር ጉዳይም አይደለም። ለዚህም ሁለት መፍትሔ አለው፦

አንደኛ ይህንን ሓቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጋዜጣ፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን አዘውትሮ ማስረዳት። ሕዝብ ዋነኛ ጠላቱ ማን እንደሆነ ለይቶ እንዲያውቅ ማድረግ፣ በኢሳት ይሁን በሌላም የብዙሓን መገናኛ በሚቀርብ የሓሰት ወሬ የማይበገር ብርቱ ዜጋ ለማፍራት፣ መፍትሔው በመንግሥት እጅ ባሉት የብዙሓን መገናኛ ዘዴዎች ተጠቅሞ ሕዝብን ማስተማርና ማንቃት ይገባል።

ይህ ግን ሁለተኛ ክንፍ እንዲኖረው ያስፈልጋል፣ ሁለተኛውም ክንፍ እንደ ኢሳት የመሰለ፣ ወይም ከዚያ የበለጠ ብርቱ የዓለምአቀፍ የተሌቪዥን አውታር ዘርግቶ፣ ኢሳት ሆነ ሌሎች ቡድኖች የውሸት ፕሮፓጋንዳቸውን ሲነፉ፣ ውሸቱን አጋልጦ በመላ ዓለም ላሉት ኢትዮጵያውያንና ለሎችም ወገኖች ሓሰቱን በመቃወምና እውነቱን አጉልቶ በማቅረብ መታገል ነው። የሓሰት ፕሮፓጋንዳ ሲደጋገም መንግሥት ምንም መልስ ሳይሰጥ ከቀረ፣ ሰሚው፤ “እውነት መሆን አለበት” ብሎ ይቀበለዋል። በሰሚውም መፍረድ አይቻልም። ስንፍናው ከመንግሥት ነው።

ይቀጥላል…

ገ/ኢ. ጐርፉ።